# የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ባለቤትና ተጠቃሚ ማነው?

**ስሜ---- ከአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ**

በቤንሻንጉል ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከሱዳን ጠረፍ 40 ኪ/ሜ ርቀት ላይ በምትገኘውና ጉምባዲ በምትባለው አካባቢ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ የመሠረት ድንጋይ የካቲት 24/2003 ዓ.ም ተጥሏል፡፡ የጣናን እጥፍ የሚሆን ሰው ሰራሽ ሀይቅ የሚፈጥረው ይህ ግድብ 5250 ሜጋዋት ኃይል የማመንጨት አቅም አለው፡፡ ከተፋሰሱ ሀገሮች ሁሉ ግብፅ በፈጠረችው ዓለም አቀፋዊ ጫናዎች ምክንያት ግንባታው የዘገየ ግድብ በኢትዮጵያውያን አቅም ሊገነባ እነሆ የመጀመሪያው ምዕራፍ ተገልጧል፡፡ የግድቡ የመሠረት ድንጋይ ከተቀመጠ በኋላ መላው ኢትዮጵያውያን በተለያየ መንገድ ድጋፋቸውንና ለግንባታው እውን መሆን በቀጣይ የሚያደርጉትን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እየገለጹ ይገኛሉ፡፡ የዓለም አቀፉን ህብረተሰብ ጨምሮ የተለያዩ ወገኖችንና ተቋማትን ትኩረት ስለሳበው  ግድብ ከየካቲት 24/2003 ጀምሮ በተለየ መልኩ በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም በተለይ በኢትዮጵያና በግብፅ የተለያዩ ዘገባዎች እየወጡ ነው፡፡

ይህን ጽሁፍ ለመፃፍ ያነሳሳኝ ዋነኛው ምክንያት ግን በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚወጡት ግድቡን የተመለከቱ አጠቃላይ ጉዳዮች ሳይሆኑ የነፃው ፕሬስን የመፃፍ ነፃነት እንደ ሽፋን በመጠቀም አንዳንድ የአገራችን ጋዜጦች የግድቡን ጠቀሜታና የባለቤትነት ጉዳይ በማይመስልና በሚያስገምት መንገድ ማስነበባቸው ነው፡፡ አባይን በ80 ቢሊዮን ብር መገደብ ቀላልም ከባድም፣ የሚቻልም የማይቻልም፣ ነው በሚል ርዕስ ሥር የተፃፈ አንድ ዘገባ ምን ይል መሰላችሁ?

አሁን መንግሥት ከያዛቸው አጀንዳዎች ሁሉ ቀዳሚው የመልካም አስተዳደር የህግ የበላይነትና የዴሞክራሲ መብቶች መከበር እንጂ የሚሊኒየም ግድብ መሆን የለበትም፡፡ እነዚህ የህዝብ ጥያቄዎች ባልተመለሱበት ሁኔታ ኢህአዴግ ግንባታውን በተገቢው መንገድ ማከናወን የማይቻለው ነው፡፡ይልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አንስቶ ‹‹ይህን ግድብ ገድቦ ለውጤት ማብቃት ከኢህአዴግ በላይ ህዝብን ይመለከተዋል›› ይላል፡፡ ቀጠል ያደርግና ደግሞ ኢህአዴግ አባይን እገድባለሁ ስላለ በኢህአዴግ ዙሪያ የሚሰበሰብ ህዝብ የለም ወዘተ…… የሚል ይዘት ያለው በተቃርኖ የተሞላ አምታችና ሃላፊነት የጎደለው/ ይቅርታ

ሃሳብ ፤አስተያየት ወይም ትችት ልለው ለራሴ ሰለሚከብደኝ ነው/ እንቶ ፈንቶ ነገር ያነሳል፡፡

በመሰረቱ አባይንና ኢትዮጵያውያንን መሠረት አድርገን ከተነሳን የግድቡ ባለቤትም ሆነ ተጠቃሚ መላው ኢትዮጵያውያኖች ነን፡፡ ሲጀመር ፀሀፊው  የዘነጉት ነገር የግድቡን የመሠረት ድንጋይ ያኖረው ኢህአዴግ ሳይሆን በህዝብ የተመረጠው መንግሥት መሆኑን ነው፡፡ መንግሥቱ ደግሞ የህዝብ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ  የመሠረት ድንጋዩን ባኖሩበት ወቅትም ሆነ ግድቡን አስመልክቶ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት የወከሉት መንግሥትን እንጂ ኢህአዴግን አልነበረም፣ አይደለምም፡፡ ፓርቲና መንግሥትን መለየት ያልተቻለበት ምክንያት የመረዳት ሳይሆን ዓላማው ሌላ ነው፡፡ ዳሩ ግን ሕዝቡ የነዚህን መሰሪዎችና የበግ ለምድ ለባሾች ድብቅ አጀንዳ መለየት የሚያስችል ፖለቲካዊ እውቀት ያዳበረና የነቃ ስለሆነ ሀቁን በሚገባ ተረድቶታል፡፡ ለዚህም ቁርጠኝነቱንና የዓላማ ጽናቱን ገና ከጧቱ በተግባር እያሳያቸው ነው፡፡ በእርግጥም መላ ዜጎችን የሚያኮራ ታላቅ የህዝብ ተነሳሽነት እየተነጸባረቀበት ያለ በመሆኑ እኛን ብቻ ሳይሆን መላ ዓለምን ያስደመመ ድንቅ እንቅስቀቃሴ፡፡

ሌላው ከመልካም አስተዳደርና ከህግ የበላይነት ጋር ተያይዞ ላሉት ችግሮች  የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ቀዳሚ አጀንዳ ሊሆን አይገባም በሚል ከአንዳንድ ስውር አጀንዳቸውን ለማራመድ ከሚጥሩ ጸረ ልማት ኃይሎች ጎራ ባዶ ዋይታ መስማት በእጅጉ አስገራሚ ነው፡፡ በኢህአዴግ የሚመራው መንግሥት መልካም አስተዳደርንና የህግ የበላይነትን የማስፈን ጥረት የእለት ከእለት ተግባሩ አድርጎ የያዘው ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ረገድ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትና የተገኙ ስኬቶችን በዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለነዚህ መብቶች መረጋገጥ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ ያም ሆኖ ግን ከምንፈልገው ደረጃ ላይ ደርሰናል ተብሎ ስለማይታሰብ ይህ ሥራ ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚካሄድና ትልቅ ትኩረት የተሰጠው መሆኑ በግልጽ ይታወቃል፡፡

ሁሌም ቢሆን ስል ህግ የበላይነት፤ መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ስናነሳ ራሳችንን ከሂደቱ አስወጥተን ሳይሆን ጉዳዩ የኛም የገዢውም ፓርቲ፣ የመንግሥትም፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎችም፣ የመንግሥትም ሆነ የግሉ የሚዲያ ተቋማትም ጭምር  መሆን ይገባዋል እንጂ መሸቶ በነጋ ቁጥር ኢህአዴግ ነው ብሎ መጮህ ከእውነታው ጋር መጋጨት ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ለነዚህ መብቶች መረጋገጥ ገዢው ፓርቲ ተግቶ እየሰራ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የሚቻልባቸው በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ባለፉት ዓመታት

የተገኙት የልማት ውጤቶች እኮ የዚሁ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የተደረገው ጥረት ውጤቶች ናቸው፡፡‹‹ያለመልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ልማት የማይታሰብ ነው›› በሚለው መርህ ከተስማማን የተገኘው የልማት ውጤት ምንጩን ለመረዳት አስረጂ ሊያሻን አይገባም፡፡ ነገር ግን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በራሱ ሂደት ከመሆኑ አንጻር ገና ብዙ የሚቀሩት የቤት ሥራዎች ስለመኖራቸው ማሰብ ይቻላል፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታትና ከግድቡ የመሠረት ድንጋይ ማኖር አስቀድሞ እኮ በኪራይ ሰብሳቢ ባለሀብቶችና አመራሮች ላይ የተወሰደው እርምጃ የገዢውን ፓርቲ ቁርጠኝነት የሚያሳይ እንጂ የአጀንዳ ማስቀየሻ ነው ተብሎ የሚወሰድ ሊሆን አይችልም፤አይደለምም፡፡ አጀንዳችንማ አንድና አንድ ብቻ ነው--ልማት፤አሁንም ልማትና ከድህነት ፈጥኖ መላቀቅ-አለቀ፡፡

የምንጽፈው በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርተን ከሆነ ዓላማችን ደግሞ የጐበጠው እንዲቃና የተቃናው ደግሞ የበለጠ እንዲቃና ለማሳየት ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን የተቸናቸውንና የጠየቅናቸውን ጥያቄዎች የሚመለከተው አካል ተገንዝቦ ሲያስተካክል ሌላ ታርጋና ምክንያት መደርደር የጤና አይመስለኝም፡፡ ምናልባትም “በአንድ እራስ ሁለት ምላስ እንዲሉ” ከኢህአዴግ በላይ ለግድቡ ህዝቡ ያገባዋል የሚለን ፀሀፊ መልሶ “የሀገርህ ባለቤት ስላልሆንክ ድጋፍ ማድረግ አይጠበቅብህም” ሲል አያሳፍርም? ዳሩ የግድቡን የባለቤትነት መብት ለኢህአዴግ ከሰጠ ፀሀፊ ከዚህ በላይ መጠበቅ የዋህነት ነው፡፡ በጣም አስገራሚው ነገር ደግሞ የሰሜን አፍሪካ አመጽ በኢትዮጵያ እንዳይደገም መንግሥት የአባይን ግድብ የሕዝብ ትኩረት ማስቀየሻ አድርጎ ያቀረበው ነው በሚል የተሰነዘረው ማደናገሪያ ነው፡፡ ግድብ ይቅርና አንድን አነስተኛ ፕሮጀክት ለማጥናትና ወደ ሥራው ለመግባት እንኳ የወራት ወይም የዓመታት የዝግጅት ጊዜን ይጠይቃል፡፡ ከዓመታት በላይ ጊዜ እንደወሰደ መገመት የሚቻለውን ይህን ግዙፍ የፕሮጀክት ጥናት /በሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ ፈጽሞ ሊታሰብ ለማይችል/ የሕዝብ አመጽ ማምከኛነት “በስጦታ” የቀረበ ነው ብሎ መፃፍ ያሳፍራል፡፡ ከዚህ ይልቅ ፕሮጀክቱ በእርግጥም ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የቀረበ ታላቅ የልማት ውጥን እንደሆነና ይህንንም ራሱ ሕዝቡ በባለቤትነት መንፈስ እንደሚያሳካው ወዳጅም ጠላትም ሊረዳው ይገባል፤ይህ ደግሞ ነባራዊ ሁኔታ ነው፡፡

በናይል ተፋሰስ አገሮች መካከል ትብብር ለመፍጠር እ.ኤ.አ በ1998 በዳሬ ሰላም የተቋቋመው ናይል ቤዚን ኢንሼቲቭ አላማ ከዚህ ቀደም የተደረጉና የተሳሳቱ ስምምነቶችን በተለይ የግርጌ ተፋሰስ አገሮቹ በሌሎቹ ላይ የነበራቸውን ተጽእኖ በማስቀረት ፍትሀዊ ተጠቃሚነትን ለመዘርጋት ነው፡፡ ይህን ለ11 ዓመታት የተደረገ የትብብር ስምምነት ጥረትና ታሪካዊ ዳራ ብቻ ብናይ ዓላማው ሁሉንም የውሃውን ባለድርሻዎች ፍትሃዊ

ተጠቃሚነት በጋራ የትብብር መንፈስና የሕዝብ ለሕዝብ ቅርርብ ለማረጋገጥ እንደሆነ በግልጽ ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳ በይበልጥም በግብጽና ከዚያም መለስ ባለ ሁኔታ በሱዳን ወገን ይህ ጥረት ባይደገፍም በሌሎች የተፋሰሱ ሃገራት ዘንድ ግን ሰፊ ይሁንታን አግኝቷል፡፡ ለፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም መስፈንና መረጋገጥ ኢትዮጵያ እየተጫወተችው ያለው ገንቢ ሚና የጎላ ስለሆነ ይህ ጥረቷ በሌሎች ባለድርሻዎች ዘንድም እውቅና እየተቸረው መጥቷል፡፡

የመሠረት ድንጋዩ በተቀመጠበት እለት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲናገሩ የግንባታውን 50 በመቶ ይህል ወጪ ግብፅና ሱዳን ሊሸፍኑ ይገባቸው እንደነበረ አስምረውበታል፡፡ ይህም የራሱ ምክንያት አለው፡፡ ከዚህ ግድብ የራሳችን ተጠቃሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከፊል የተጠቃሚነት ድርሻ ግን የግብፅና የሱዳን እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡ ምክንያቱም ግብጽ ውስጥ በትነት የሚባክነውን ውሃ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ፣ በደለል መሙላት ምክንያት ሱዳንን ሁሌ የሚያስጨንቀውን ጐርፍ ለመከላከል፣ግድቡ ከሚመነጨው ኃይልም በተመጣጣኝ ክፍያ ተጠቃሚዎች ሊሆኑ ስለሚችሉ ወዘተ የህዳሴ ግድብ መፍትሔ ነው፡፡

በአባይ ላይ የተዛባ አስተሳሰብ የነበራቸው አንዳንድ ግብፃውያን የግድቡ ጠቀሜታ የጋራ መሆኑን ተገንዝበው መንግሥታቸው በዚሁ የትብብር መንፈስ ብቻ እንዲጓዝ በመጠየቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ ጽንፈኛ አቋም ያላቸው ግብፃውያን ምንም እንኳን ብዙዎች ግንዛቤያቸው የተሳሳተ ቢሆንምና ሃቁን ለመረዳት ባይፈልጉም የጋራ ጉዳያቸው የሆነውን አባይን በተመለከተ ግን ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የግል ፕሬሶች፣ ሌላውም የህብረተሰብ ክፍል በአንድነት እየተንቀሳቀሱ ስለመሆኑ ወደ ዩጋንዳ የተጓዘውን የግብጽ ልኡካን ልብ ይሏል፡፡ በለየለት ጭፍን ተቃውሞ የነበዙና ምንጊዜም ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥቅም በተጻራሪ ለመቆም ተማምለው በቃል ኪዳን የተሳሰሩ የኛዎቹ አንዳንድ ጉዶች ግን "የእናት ሆድ ዥጉርጉር" እንዲሉ ፍፁም አስተውሎት በጐደለው መንገድ የያዙት አቋም በእጅጉ አሳዛኝ ነው፡፡ አንዳንድ የግብጽ ምሁራን፣ባለሥልጣናት፣ፕሬሶችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በአባይ ጉዳይ አበረታች ሊባል በሚችል ደረጃ የአቋም ለውጥ ወይም ቢያንስ የመለሳለስ አዝማሚያ እያሳዩ ባለበት ሁኔታ የእነዚህ "ዜጎች " ብለን ልንጠራቸው የምናፍርባቸው አንዳንድ ሰዎች በዚህ ሃገራዊ አጀንዳ ላይ የሚያንጸባርቁት አቋም ግን በእጅጉ ሊፈተሽ ይገባዋል፡፡ ሃገራዊና የትውልድ ኃላፊነት የጎደላቸው እነዚህ ወገኖች እያራመዱት ያለው የለየለት የጠላትነት አቋም የትም ሳይደርስ እንደ ጧት ጤዛ በራሱ ተንኖ እንደሚጠፋ ግን በፍጹም እርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ምክንያቱም መላ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለእቅዱ

መሳካት የተፈለገውን ሁሉ መስዋእትነት እንደሚከፍሉ ገና ከጧቱ ቁርጠኝነታቸውን እያረጋገጡ ነውና፡፡

እነዚህ ጉደኞች ወደዱም ጠሉም ግን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ‹‹የአዲስ ዘመን ብሥራት›› ሆኖ እነሆ ልክ እንደ አባይ ፍሰቱን ቀጥሏል፡፡ መላው የአገራችን ህዝቦችና ተቋማት እንዲሁም በርካታ ፕሬሶች እጅግ በሚያስመሰግን ሁኔታ ለስኬቱ የድርሻቸውን እየተወጡ ነው፡፡ እንዴት? ብዙዎች የፕሬስ ውጤቶች ዘላለም ስንዘምርለት ለነበረው የአባይ ውሀ ልማት ዛሬ ደግሞ ገድል መፈፀም የሚገባን እንደሆነ በማብሰርና ከፍተኛ የሕዝብ ንቅናቄ በመፍጠር ረገድ እየተጫወቱት ያለው ገንቢ ሚና በእጅጉ ሊመሰገን ይገባል፡፡ ኢትዮጵያውያንም የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ 80 ቢሊዮን ብር ‹‹ለአንድ ሰው ሸክም ለ80 ሚሊዮናችን ደግሞ ጌጥ ነው›› ብለው በየደረጃው ተነስተዋል፡፡ በእጅጉ ያስደነቀኝና ስሜቴን የነካኝ ደግሞ የተማሪዎች ነው፡፡ በአንድ ት/ቤት በክፍል ደረጃ ብር 12፡50ሣ በነፍስ ወከፍ አዋጥተው ቦንድ የገዙ ተማሪዎችን ዜና ከሚዲያዎች አዳምጠናል፡፡ አኩሪ ተነሳሽነትና ተሳትፎ በመሆኑ እነዚህን ብርቅዬና ሃገር ተረካቢ ትውልዶች እደጉ ተመንደጉ አልኳቸው፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ለልጆቻችን ምን አይነት አኩሪ የታሪክ ውርስ እያስቀመጥን እንደሆነና ነገ ደግሞ ቀጣዩ ትውልድ በምንተውንለት ቅርስ የሚኮራ መሆኑንና ስማችንንም በኩራት እያነሳ ለትውልድ እንደሚያስተላልፍ ሳስብ የዜግነት ኩራት ተሰማኝ፡፡

ሉአላዊነትን ለማስከበር የነበረው መተባበር አሁን በላቀ ደረጃ በልማቱ ሲደገም ይህ የመጀመሪያ ጊዜ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይሄ ሃገራዊ እንቅስቀሰሴም መላው ዓለም አድናቆቱን እንዲቸር አስገድዶታል፡፡ ዲያስፖራውም እኛም አለን እያለ ነው፡፡ ይኼ ብቻም ለኢትዮጵያውያን በቂ ሆኖ አልተገኘም ደስታቸውንና ቁርጠኝነታቸውን በሰላማዊ ሰልፍ በመግለጽ ላይ ናቸው፡፡ ከጅማሬው ላይ እየታየ ያለው ታላቅ ሃገራዊ መነቃቃትና ተነሳሽነት በግልጽ እንደሚያሳየንም የሚሊኒየም ግድብ ግንባታችን ፍፃሜው ያማረ እንደሚሆን አንጠራጠርም ‹‹የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል›› እንዲሉ፡፡ አበቃሁ፡፡